በግብርናና እንስሳት ሀብት ሚኒስቴር
በግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት
የአርዳይታ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ
<u>አዲስ አበባ</u>

ጉዳዩ፡- **<u>የኮሌጁን የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት የመጨረሻ</u>**
<u>የሥራ አመራር ሪፖርትን ይመለከታል</u>፤

በርዕሱ የተጠቀሰውን የአርዳይታ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ የ2009 በጀት ዓመት ሂሣብ የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦችን የያዘ 27 ገጽ የመጨረሻ የሥራ አመራር ሪፖርት (Final Management Letter) እና 17 ገጽ አባሪ በድምሩ 44 ገጽ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አያይዘን ልከናል። በመሆኑም በገጽ 45 በተመለከተው የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች አተገባበር መርዓ-ግብር ቅጽ መሰረት የተወሰዱ እርምጃዎች በአስቸኳይ እንዲላክልን እናሳስባለን።

ከሰላምታ ጋር !

ሰለሞን መብራቱ
የልማትና ማኅበራዊ መሥሪያ ቤቶች
ኦዲት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

<u>ግልባጭ</u>

- ☞ ለግብርናና እንስሳት ሀብት ሚኒስቴር ከ45 ገጽ አባሪ ጋር
- ☞ ለግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ማስተባበሪያ
- ☞ ጽህፈት ቤት ከ45 ገጽ አባሪ ጋር

<u>አዲስ አበባ</u>

በግብርናና እንስሳት ሀብት ሚኒስቴር

በግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮጀክት ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት

የአርዳይታ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ

የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት

የመጨረሻ የሥራ አመራር ሪፖርት

ግንቦት 2010 ዓ.ም

አዲስ አበባ

በግብርናና እንስሳት ሀብት ሚኒስቴር

በግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮጀክት ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት

የአርዳይታ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ

የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት የመጨረሻ የሥራ አመራር ሪፖርት

መግቢያ

ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ በአዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመሥሪያ ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሰረት በቀድሞው እርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር የ2009 በጀት ዓመት የሂሣብ መግለጫ ላይ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለን ዘንድ የአርዳይታ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ ሂሳቡን ኦዲት አድርገናል፡፡

ዓላማ

የዚህ ደብዳቤ ዓላማ በኦዲታችን ወቅት የተገኙት የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እና ሌሎች ግድፈቶችን ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ፣ የፕሮጀክት ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤቱና የኮሌጁ የበላይ አመራር አካላት እንዲያውቁትና ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስዱበት ለማድረግ ነው፡፡

የኦዲቱ ወሰንና ኃላፊነት

ኦዲቱ የተከናወነው የዓለም አቀፍ የመንግሥት ኦዲት ደረጃዎችን (INTOSAI/ISA) መሰረት በማድረግ እና የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤትን የኦዲት ሥልት በመከተል ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አጥጋቢ የሆነ ማረጋገጫ (የኦዲት አስተያየት) ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን የሚያካትተው፡-

- ✓ በሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩት አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና መመርመርን፣
- ✓ የሥራ አመራሩ የሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረጋቸው ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎች መመዘንን፣

- ✓ የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ለፌዴራል መንግሥት አጠቃላይ ዓመታዊ ገቢና ወጪ ሂሣብ መግለጫ ዝግጅት አግባብነት ያላቸው መሆኑን፣ ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የሂሳብ መግለጫዎቹ ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና መመርመርን ይጨምራል፡፡
የሂሳብ መግለጫዎቹ ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆናቸው በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል፡፡ አስተያየት ላይ ለመድረስ በሂሳብ መግለጫዎች ላይ ያለውን የመረጃ አቀራረብ አጠቃላይ ብቃት ገምግመናል፡፡

በመሆኑም በዚህ ሪፖርት ላይ ከተመለከቱት የአሰራርም ሆነ የሂሳብ አያያዝ ድክመቶች በተጨማሪ ሌሎች ድክመቶች ወይም ስህተቶች ሊኖሩ የሚችሉ ከመሆኑም በላይ የሂሳብ መግለጫውን ለማዘጋጀት የተዘረጉትን የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም፡፡

የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ከዚህ ጋር የተያያዙ ግድፈቶችና ስህተቶች ሁሉ ሊታወቁ የሚችሉት ይህን አስመልክቶ ሰፊ ጊዜ በመውሰድ ልዩ የዝርዝር ኦዲት በጥልቀት ሲከናወን መሆኑን እንገልጻለን፡፡

የሂሳብ መግለጫዎችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የአርዳይታ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ መግለጫዎችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ኃላፊነት ነው፡፡

የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሐሳቦች

የአርዳይታ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ በ2009 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሐሳቦች ረቂቅ ሪፖርት ላይ ምላሽ እንዲሰጥ የካቲት 13 ቀን 2010 ዓ.ም በቁጥር OFAGF-02.1/2/13 በተጻፈለት ደብዳቤ መሰረት ኮሌጁ የካቲት 20 ቀን 2010 ዓ.ም በቁጥር 273/አር/ኮ/6-6 እንዲሁም መጋቢት 5 ቀን 2010 ዓ.ም በቁጥር 274/አር/ኮ/6-6 በተጻፉ ደብዳቤዎች ምላሽ ሰጥቷል። በመሆኑም ለሥራ አመራሩ የተዘጋጀው የመጨረሻው ሪፖርት እንደሚከተለው ቀርቧል።

1. የገቢ ሂሳብ

1.1. የሂሳብ መደቡን ጠብቆ ያልተመዘገበ የገቢ ሂሳብ፤

1.1.1. ግኝት

የገቢ ሂሳቦች የሚመዘገቡት የገ/ኢ/ል/ት/ሚ/ር ነሐሴ 1999 ዓ.ም ባወጣው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ኮሌጁ በበጀት ዓመቱ ከሲኦሲ (COC) ምዘና የሰበሰበውን ገቢ በ1443 መመዝገብ ሲገባው በጠቅላላው ብር 21,000.00 በሂሳብ መደብ 1489 የመዘገበ መሆኑ ታውቋል። (ዝርዝሩ አባሪ 1 ተያይዟል)

1.1.2. ሥጋት

- በሂሳብ መግለጫው ላይ በየሂሳብ መደቦቹ ሥር ሊታይ የሚገባውን የሒሳብ ሚዛን ሊያዛባው ይችላል።
- ለሂሳብ ሪፖርቱ ተጠቃሚዎች ትክክለኛ መረጃውን እንዳይሰጥ ሊያደርግ ይችላል።

1.1.3. የማሻሻያ ሃሳብ

በትክክለኛዉ የሂሳብ መደብ ላልተመዘገበው ሒሳብ ተገቢው ማስተካከያ እንዲሰራለት፤ ለወደፊቱም ኮሌጁ የሂሳብ ምዝገባ ሲያከናውን የገ/ኢ/ል/ት/ሚ/ር ነሐሴ 1999 ዓ.ም ያወጣውን የሂሳብ አያያዝ ሥርዓትን ተከትሎ ምዝገባወን ማከናወን ይኖርበታል።

1.1.4. ***የሥራ አመራሩ ምላሽ***

የተሰጠውን የማሻሻያ ሃሳብ በመቀበል ወደፊት በደንቡና በመመሪያው መሰረት የሚፈጸም መሆኑን እንገልጻለን።

2. **ተሰብሳቢ ሂሳብ**

2.1. **በደንቡና በመመሪያው መሰረት ያልተወራረደ (ያልተሰበሰበ) ሂሳብ፤**

2.1.1. **ግኝት**

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 እንዲሁም በፌዴራል የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 4/2003 መሰረት ለውሎ አበልና ለመጓጓዣ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ ሰራተኛው ሥራውን አጠናቆ ከተመለሰ በኋላ፤ በመመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት ደግሞ ለግዥ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ በሰባት ቀናት ውስጥ መወራረድ እንዳለበት ያዛል። ይሁንና ኮሌጁ በደንቡና በመመሪያው መሰረት የፈጸመ መሆኑ ሲጣራ በተለያዩ የተሰብሳቢ የሂሳብ መደቦች (ኮዶች)፡-

- ከአንድ ወር እስከ አንድ ዓመት ድረስ የቆየ ብር 62,582.88፣
- ከአንድ ዓመት በላይ እስከ አምስት ዓመት ድረስ የቆየ ብር 81,428.77፣

በድምሩ ብር 144,011.65 በደንቡ መሰረት ሳይወራረዱ (ሳይሰበሰብ) በሂሳብ መግለጫው ላይ የሚታይ መሆኑ ታውቋል። በተወሰኑት ሂሳቦች ላይ በ2008 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ወቅትም ሂሳቡ እንዲወራረድ አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም በአሁኑ ኦዲት ወቅትም ሂሳቡ ሳይወራረድ ይገኛል። (ዝርዝሩ አባሪ 2 ተያይዟል)

2.1.2. ***ሥጋት***

በተሰብሳቢ ሂሳቦች ላይ ተገቢው ቁጥጥርና ክትትል ካልተደረገ፡-

- የመንግሥት ገንዘብ ሳይሰበሰብ ሊባክን ይችላል።

♦ ገንዘቡ ለታለመለት ዓላማ መዋሉን ለማረጋገጥ አይቻልም።

2.1.3. የማሻሻያ ሃሳብ

የቅድሚያ ክፍያ ሒሳቦች በመንግሥት የፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሰረት እንዲወራረዱ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል። ሊሰበሰቡ የማይችሉ ከሆነ ደግሞ ሁኔታው ተጣርቶ ደንብና መመሪያውን ተከትለው እንዲሰረዙ መደረግ እንዳለበት በድጋሚ ለማሳሰብ እንወዳለን።

2.1.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ

- በበጀት ኮድ (መደብ) ቁጥር 4274 የሚታየው የተሰብሳቢ ሂሳብ ግኝት ትክክል ነው። ይህም በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ (የቀድሞ ግብርና ሚኒስቴር) እና በስሩ በሚገኘው የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት መሥሪያ ቤት በዱቤ ለተሰጠው የስንዴ ሂሳብ ሲሆን ገንዘቡን እንዲያስገቡ በተደጋጋሚ ጊዜ ለሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ብንጽፍም ምላሽ ያልተሰጠበት ቢሆንም እስከ አሁንም ድረስ ለእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴርም በተመሳሳይ ደብዳቤ ጽፈን ምላሹ በመጠበቅ ላይ እንገኛለን።
- በበጀት ኮድ (መደብ) ቁጥር 4203 ላይ የተመለከተውም በተመሳሳይ በ2008 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ወቅት አስተያየት ከተሰጠበት በፊትና በኋላም በፍርድ ቤት የተያዘና ውሳኔ ያልተሰጠው ሆኖ ችግሩ ከአቅም በላይ በመሆኑ በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በኩል እንዲሰረዝ (Right Off) እንዲደረግ ደብዳቤ ተጽፎ ምላሽ በመጠበቅ ላይ ይገኛል። ውሳኔው እንደደረሰን የሚስተካከል ይሆናል።

2.1.5. የኦዲተሩ አስተያየት

አብዛኞዎቹ ተሰብሳቢዎቹ ለረዥም ዓመታት ሲንከባለሉ የቆዩ ሲሆን፣ ባለፉት በጀት ዓመታት ኦዲት ወቅትም መወራረድ (መሰብሰብ) የሚችሉት እንዲወራረዱ (እንዲሰበሰቡ)፤ መወራረድ (መሰብሰብ) የማይችሉ ከሆነ ደግሞ በደንቡና በመመሪያው መሰረት አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ አስተያየት የተሰጠባቸው ቢሆንም ተገቢው እርምጃ ባለመወሰዱ ተሰብሳቢ

ሒሳቦቹ ከዓመት ወደ ዓመት እየተንከባለሉ ይገኛሉ፡፡ ስለሆነም በተሰጠው የማሻሻያ ሃሳብ መሰረት እርምጃ እንዲወሰድ፤ እንዲደረግ እንዲሁም ሒሳቡን ለማወራረድ እየተደረገ ያለው ጥረትም ተጠናክሮ እንዲቀጥል እናሳስባለን፡፡

3. <u>ተከፋይ ሂሳብ</u>

3.1. <u>በወቅቱ ያልተከፈለ ወይም የተከፋይ ሂሳቡ ሁኔታ ተጣርቶ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ ያልተደረገ ሂሳብ</u>፤

3.1.1. <u>ግኝት</u>

በኮሌጁ የሚገኙት ተከፋይ ሂሳቦችን ተገቢነት ለማረጋገጥ እንዲሁም መሥሪያ ቤቱ ያለበትን ተከፋይ ሂሳብ በወቅቱ ለሚመለከተው አካል የሚከፍል መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ከካፒታልና ከውስጥ ገቢ በጀት በተለያዩ የተከፋይ ሂሳብ ኮዶች (መደቦች)፡-

- ከአንድ ወር እስከ አንድ ዓመት ድረስ የቆየ ብር 34,643.49፣
- ከአንድ ዓመት በላይ እስከ አምስት ዓመት ድረስ የቆየ ብር 8,000.00፣

በድምሩ ብር 42,643.49 ሳይከፈል ለረዥም ጊዜያት በሂሳብ መግለጫው ላይ የሚታይ ሲሆን፣ በተወሰኑት ሂሳብ መደብ ላይ በ2008 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ወቅትም የሂሳቡ ሁኔታ ተጣርቶ አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም እርምጃ እንዲወሰድ ያልተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡ (ዝርዝሩ አባሪ 3 ተያይዟል)

3.1.2. <u>ሥጋት</u>

የተከፋይ ሂሳቡ ሁኔታ ተጣርቶ አስፈላጊው አርምጃ ካልተወሰደ የሂሳብ ሪፖርቱን ተዓማኒነት ሊያሳጣው ይችላል፡፡

3.1.3. <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

በፋይናንስ አስተዳደር ደንብና መመሪያ መሠረት ተከፋይ ሂሳቦች በወቅቱ መከፈል ይኖርባቸዋል፡፡ ለረጅም ዓመታት ሲንከባለል የመጣውና ለማን

እንደሚከፈል የማይታወቀው ተከፋይ ሂሳብ ሁኔታም ተጣርቶ አስፈላጊው እርምጃ ሊወሰድ ይገባል።

3.1.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ

- ለሀገር ውስጥ ገቢ መከፈል የነበረበት በተፈጠረው የበጀት እጥረት ምክንያት በወቅቱ ያልተከፈለና በ2010 በጀት ዓመት በጀቱ እንደተለቀቀ ተከፍሎ የተጠናቀቀ መሆኑን እንገልጻለን።
- ከሶስት የኮሌጁ ሰራተኞች ላይ የሚፈለግ የወጪ መጋራት ሂሳብ ሲሆን፣ እስከሚያልቅ ድረስ በየወሩ ከደመወዛቸው እየተቆረጠ ለፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ መሆኑን እንገልጻለን።

3.1.5. የኦዲተሩ አስተያየት

- ለሀገር ውስጥ ገቢ ለመደረጉ በቀጣይ ኦዲት ወቅት የሚረጋገጥ ይሆናል።
- የወጪ መጋራት ክፍያ ከሰራተኞች በየወሩ እንደተቆረጠ በተቆረጠበት ወቅት ወዲያውኑ ለሚመለከተው አካል ገቢ መድረግ ይመኖርበታል እንጂ ገንዘቡ ተሰብስቦ እስኪጠናቀቅ ድረስ መጠበቅ የለበትም። ሰለሆነም አሰራሩ እንዲስተካከል መደረግ ይኖርበታል። ለወደፊቱ በማሻሻያ ሀሳቡ በተመለከተው በፋይናንስ አስተዳደር ደንብና መመሪያ መሠረት ተከፋይ ሂሳቦች በወቅቱ መከፈል እንዲከፈሉ፤ ለረጅም ዓመታት ሲንከባለል የመጣውና ለማን እንደሚከፈል የማይታወቀው ተከፋይ ሂሳብ ሁኔታም ተጣርቶ አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ መደረግ ይኖርበታል።

4. የወጪ ሂሳብ

4.1. በተገቢው የሂሳብ መደብ ያልተመዘገበ የወጪ ሂሳቦች፤

4.1.1. ግኝት

የወጪ ሂሳቦች የሚመዘገቡት የገ/ኢ/ት/ሚ/ር ነሐሴ 1999 ዓ.ም ባወጣው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የተመዘገበ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት

ሲደረግ ብር 463,230.47 ክፍያዎች በተገቢው የሂሳብ መደብ ሳይመዘገቡ ተገኝተዋል። (ለዝርዝሩ አባሪ 4 ተያይዟል)

4.1.2. ሥጋት

- ☞ የተዘጋጀዉን የሂሳብ መግለጫ ታዓማኒነት ሊያሳጣዉ ይችላል።
- ☞ ከበጀት በላይ የወጣ ወጪ እንዳይታይ የተደረገ ሊሆን ይችላል።

4.1.3. የማሻሻያ ሃሳብ

በትክክለኛዉ የሂሳብ መደብ ላልተመዘገበው ሒሳብ ተገቢው ማስተካከያ እንዲሰራለት፤ ለወደፊቱም ኮሌጁ የገ/ኢ/ል/ት/ሚ/ር ነሐሴ 1999 ዓ.ም ያወጣውን የሂሳብ አያያዝ ሥርዓትን ተከትሎ ምዝገባውን ማከናወን ይኖርበታል።

4.1.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ

በበጀት ኮድ 6114 አንድ ካቦ ከስምንት አስከ አስራ ሁለት ሰው (በቂ) የሰው ኃይል ማቅረብ ለሚችል ስለሚከፈል ይህንን ታሳቢ በማድረግ የተከፈለ ነው። ከላይ እንደተገለጸው የበጀት ኮዱ የማይጋብዝ ከሆነ በ2011 የበጀት ዓመት ማስተካከያ ተደርጎ እንዲከፈልና እንዲመዘገብ እናደርጋለን።

4.1.5. የኦዲተሩ አስተያየት

የገ/ኢ/ት/ሚ/ር ነሐሴ 1999 ዓ.ም ባወጣው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መመሪያ መሰረት በ6114 የወጪ ሂሳብ መደብ ክፍያ የሚፈጸመው የተፈቀደ የሥራ መደብ ለሌላቸው እና የሚከፈላቸው ደመወዝ በፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር ያልጸደቁ ሰራተኞች ናቸው። እነዚህ ሰራተኞች ጊዜያዊ ሰራተኞች ሲሆኑ፣ የሥራው ሁኔታ የሚወሰነው በሚሰሩበት መሥሪያ ቤት ለመሆኑ ተመልክቷል። በ6255 የሂሳብ መደብ (ኮድ) ደግሞ መመዝገብ ያለባቸው ለመጓጓዣ፣ ለማስጫኛና ለማራገፊያ የሚወጡ ወጪዎችን ይመለከታል። ስለሆነም ምዝገባዎቹ መከናወን ያለባቸው በ6114 የሂሳብ መደብ ሳይሆን በ6255 የሂሳብ መደብ ሊሆን ይገባል።

4.2. ሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ላይ ተመዝግበው የተገኙ የጥሬ ገንዘብ ክፍያዎች ስለመኖራቸው ፤

4.2.1. ግኝት

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ትብብር ሚኒስቴር ባወጣው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሰረት የቼክ ወይም የባንክ ዝውውር የገንዘብ ክፍያን ለመመዝገብ የምዝገባ መነሻ ሰነድ በመሆን የሚያገለግለው የባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ሲሆን፣ የጥሬ ገንዘብ ክፍያ በገንዘብ ያዥ ሲፈጸም ደግሞ የምዝገባ መነሻ ሰነድ የሚሆነው የወጪ ማስመስከሪያ ለመሆኑ ተመልክቷል። በሌላ በኩል ደግሞ ጥሬ ገንዘብ ነክ ያልሆኑ የሒሳብ እንቅስቃሴዎችን ለመመዝገብ በምዝገባ መነሻ ሰነድነት የሚያገለግለው የሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ለመሆኑ በሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መመሪያው ላይ ተገልጿል። በመሆኑም ከሌጁ የሂሳብ ምዝገባውን የሚያከናውነው በሂሳብ አያያዝ ሥርዓቱ ላይ በተመለከተው መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ በናሙና ኦዲት ሲደረግ ብር 257,578.47 የጥሬ ገንዘብ ክፍያዎች የሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ተዘጋጅቶላቸው ተመዝግበው ተገኝተዋል።

(ለዝርዝሩ አባሪ 5 ተያይዟል)

4.2.2. ሥጋት

የወጪ ሂሳብ ሰነዶቹ በሂሳብ አያያዝ ሥርዓቱ ላይ በተቀመጠው መሰረት ጥቅም ላይ የማይውሉ ከሆነ የመረጃውን ተጠቃሚዎች ሊያሳስቱ ይችላሉ።

4.2.3. የማሻሻያ ሃሳብ

የጥሬ ገንዘብ፣ የቼክ ወይም የባንክ ዝውውር የገንዘብ ክፍያዎች ሲፈጸሙ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ትብብር ሚኒስቴር ባወጣው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሰረት በተገቢው የሂሳብ ሰነድ እንዲመዘገቡ መደረግ ይኖርባቸዋል።

4.2.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ

ይህ አሰራር ለረጅም ዓመታት ሲሰራበት የቆየ ቢሆንም አሁን ግን ተስተካክሎ እየሰራበት መሆኑን እንገልጻለን።

4.3. በፋይናንስ መመሪያው መሰረት ያልተመዘገበና ያልተፈጸመ የኮንትራክተር ክፍያ፤

4.3.1. ግኝት

በኮሌጁ ለህንፃ ተቋራጭ የሚፈጸመው ክፍያ በግዥ መመሪያው እና በውሉ መሰረት የተፈጸመ መሆኑን እና የአመዘጋገብ ሥርዓቱም የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ነሐሴ 1999 ዓ.ም ባወጣው የፌዴራል መንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መመሪያን ተከትሎ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ኮሌጁ የሰራተኞች መኖሪያ ቤት ግንባታ ሥራን ለማከናወን እንዲቻል ሳምሶን ገብረ ዮሐንስ ከተባለ የሕንጻ ሥራ ተቋራጭ ጋር እንዲሁም የተማሪዎች ማደሪያ ዶርሚተሪ ህንጻ ግንባታን ከማይለም ኮንስትራክሽን ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ጋር ባደረገው ሥምምነት መሰረት የተፈጸሙ ክፍያዎችና የአመዘጋገብ ሥርዓቱ መመሪያውን ተከትለው የተፈጸሙ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ቀጥለው የተመለከቱት ሁኔታዎች ታይተዋል።

1. **ማይለም ኮንስትራክሽን ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር**

   - ብር **138,751.10** ያልተመለሰ የቅድሚያ ክፍያ ተመላሽ መኖሩ፣
   - ብር **33,990.14** ያልተቀነሰ የተጨማሪ ዕሴት ታክስ መኖሩ፣
   - ብር **31,180.31** ያልተቀነሰ የመያዣ ሂሳብ መኖሩ፣
   - በተጠቀሱት ልዩነቶች ምክንያት ብር **203,921.55** በብልጫ የተከፈለ የጥሬ ገንዘብ ሒሳብ መኖሩ፣

   (ለዝርዝሩ አባሪ 6 ተያይዟል)

2. **ሳምሶን ገብረ ዮሐንስ የሕንጻ ተቋራጭ**

   በውሉ ልዩ ሁኔታዎች (Special Conditions of Contract) ክፍል 8 ንኡስ ክፍል 1.1 መሰረት ጠቅላላ የግንባታ ስራው በ365 የካሌንደር ቀናት እንደሚጠናቀቅ ቢገልጽም የግንባታ ስራው መጠናቀቅ ከነበረበት ጊዜ

ከ3 ዓመታት በላይ ከመዘግየቱም በተጨማሪም ተቋራጩ ሥራውን ሳያጠናቅቅ በ2008 በጀት ዓመት አቋርጦ የግንባታ መሳሪያዎቹን ከግንባታ ሥፍራው ያወጣ መሆኑ ተገልጾ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም የተወሰደ እርምጃ አለመኖሩ፤

(የፎቶ አባሪ ቁጥር 11 ተያይዟል)

ታውቋል።

4.3.2. ሥጋት

1. በአመዘጋገቡ ላይ በሚታየው ስሕተት ምክንያት፡-
   - ☞ የሂሳብ መግለጫው ትክክለኛውን ገጽታ እንዳያመለክት ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ።
   - ☞ ሊቀነስ የሚገባው ገንዘብ ሳይቀነስ ሊቀር ይችላል።
   - ☞ ሊከፈል የሚገባው ሒሳብ ላይከፈል ይችላል።
   - ☞ ለመንግሥት ገንዘብ ያለአግባብ መውጣት ምክንያት ሊሆን ይችላል።
2. ሥራው በውሉ መሰረት እንዲጠናቀቅ ካልተደረገ መንግሥት ለተጨማሪ ወጪ ሊዳረግ ይችላል።

4.3.3. የማሻሻያ ሃሳብ

በአመዘጋገብ ላይ ለታዩት ስህተቶች ተገቢው ማስተካከያ እንዲሰራ፤ መሰብሰብ ያለበት ሂሳብ እንዲሰበሰብ፤ መከፈል ያለበት ገንዘብ እንዲከፈል፤ ለወደፊቱም በኮንስትራክሽን ክፍያ አፈጻጸምና አመዘጋገብ ላይ ተገቢው ጥንቃቄ እንዲደረግ እናሳስባለን።

4.3.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ

- ♦ ከሳይለም ኮንስትራክሽን ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የሚፈጸመው ክፍያ ያልተጠናቀቀ በመሆኑ ወደፊት የሚስተካከል መሆኑን እንገልጻለን።

- የሳምሶን ገ/ዮሃንስ ህ/ስ/ተቋራጭን በተመለከተ የማግባባት ሥራዎች ተሰርተው ባለመሳካቱ ምን መደረግ እንዳለበት ከአማካሪ ድርጅቱ ጋር በመነጋጋር ላይ እንገኛለን።

4.3.5. የኦዲተሩ አስተያየት

1. የግንባታ ሂሳብ ክፍያ በሚፈጸምበት ወቅት ምዝገባ መከናወን ያለበት የወጡ ህጎችንና ውሉን እንዲሁም የሚቀርበውን የክፍያ ሰርተፍኬት መሰረት በማድረግ መሆን ይኖርበታል። ስለሆነም በክፍያ ወቅት ተገቢው ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል።

2. ግንባታውና ያቋረጠው ተቋራጭ በገባው ውል መሰረት ሥራውን የማያጠናቅቅ ከሆነ ኮሌጁ በህግ አግባብ የሚጠየቅበትን ሁኔታ ማመቻቸት ይኖርበታል።

4.4. ከመመሪያ ውጭ የተከፈለ ውሎ አበል፤

4.4.1. ግኝት

ኮሌጁ ለመስክ ስራ ለሚወጡ ሰራተኞች የሚፈጽመው የውሎ አበል የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ሰኔ 29 ቀን 2004 ዓ.ም በቁጥር ሲሰሚ/30/ጠ13/40/883 ባወጣው የውሎ አበል አከፋፈል መመሪያ መሰረት ማንኛውም የመንግሥት ሰራተኛ ከመደበኛ የስራ ቦታው ውጭ ወደ ሆነ ሌላ የስራ ቦታ ለስራ ጉዳይ ሄዶ ዕለቱን መመለስ ካልቻለ በአዲሱ የውሎ አበል አከፋፈል መመሪያ መሰረት ቁርስ፣ ምሳና እራት በተጠቀመበት ቦታ (ከተማ) እንዲሁም የአልጋ ክፍያ በጉዞ ወቅት ባደሩበት አካባቢ በወጣው የውሎ አበል አከፋፈል መሰረት በዝርዝር ታስቦ እንዲከፈል መመሪያው ያዛል። ኮሌጁ በዚሁ መሰረት የፈጸመ መሆኑን ለማረጋገጥ በናሙና ኦዲት ሲደረግ፡-

- አስራ አንድ የኮሌጁ ሰራተኞች በምርታማነት ማሻሻያ ማዕከል የሾፌር መካኒክነት ሥልጠና አዲስ አበባ በመሄድ ለ12 ቀናት የሰለጠኑ መሆኑን ከተሠጠው የምስክር ወረቀት መረዳት ተችሏል። ሆኖም ኮሌጁ በመንገድ ላይ ደርሶ መልስ ጎዞ የአራት ቀን የውሎ አበል ታስቦ

የአስራ ስድስት ቀን ዉሎ አበል በውሎ አበል መከፈል ሲገባው የ28 ቀን የዉሎ አበል ክፍያ በመፈጸሙ ምክንያት ያለአግባብ የአስራ ሁለት ቀን የውሎ አበል ብር 17,754.00 ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፣

- በመመሪያው መሰረት በጉዞ ወቅት ቁርስ፣ ምሳ እና እራት በደረሰበት አከባቢ ወይም ስፍራ መታሰብ ሲኖርበት ወጥ በሆነ በአዲስ አበባ ውሎ አበል የተከፈለ መሆኑ፣

ታውቋል። (ለዝርዝሩ አባሪ 7 ተያይዟል)

4.4.2. ሥጋት

የውሎ አበል ክፍያ የወጣውን መመሪያ ተከትሎ ካልተፈጸመ፡-

- የመንግሥት ገንዘብ አለአግባብ ወጪ ሊሆን ይችላል።
- የክፍያውን ትክክለኛነትና አግባብነት ለማረጋገጥ አይቻልም።
- ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል።

4.4.3. የማሻሻያ ሃሳብ

ከደንብና መመሪያ ውጪ የተፈጸመው ክፍያ በአስቸኳይ ተመላሽ እንዲደረግ፤ ለወደፊቱም የውሎ አበል ክፍያ የወጣውን መመሪያ ተከትሎ እንዲፈጸም እንዲሁም ክፍያው መመሪያው በሚፈቅደው አግባብ ለመፈጸሙ ተገቢው ቁጥጥርና ክትትል እንዲደረግ እናሳስባለን።

4.4.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ

በወቅቱ የ11 ሰዎች ሥልጠና ብቻ ሳይሆን ሌሎች 3 ባለሙያዎች ለአንድ ወር የተካተተና የሥልጠና ማዕከሉ ኘሮግራሙን በማሸጋሸጉ ከበጀት ኮድ 6271 ላይ የተከፈለ መሆኑን እየገለጽን ለወደፊቱ እናስተካክላለን።

4.4.5. የኦዲተሩ አስተያየት

የቀረበው ግኝትና የተሰጠው ምላሽ አይገናኝም። ስለሆነም ከየትኛው የበጀት ኮድ ክፍያው ከመምሪያው ወጪ መፈጸም የለበትም። ስለሆነም አለአግባብ የተፈጸመው የውሎ አበል ክፍያ በአስቸኳይ ተመላሽ መደረግ ይኖርበታል።

4.5. <u>ለኮሌጁ ክበብ የተሰጠ የገንዘብ ድጎማ</u>፤

4.5.1. <u>ግኝት</u>

ኮሌጁ ለፈጸማቸው ክፍያዎች በፌዴራል መንግሥት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት ተራ ቁጥር 6 መሰረት የተፈቀደ በጀት ለመኖሩ፣ የተሟላ ማስረጃ የቀረበላቸው ለመሆኑ እና የክፍያውን አግባብነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ሰኔ 23 ቀን 2009 ዓ.ም የኮሌጁ የስፖርትና መዝናኛ ክበቡ ለኮሌጁ በጻፈው ደብዳቤ በኮሌጁና በአካባቢው ወረዳው ከባለፈው አጋማሽ አመት ጀምሮ ተከስቶ በነበረው የፀጥታ ችግር የኮሌጁንና የአከባቢውን ፀጥታ ለማስከበር የመጡ የመከላከያ አባላት፣ የኦሮሚያ ፖሊስ ሠራዊት አባላትና የወረዳችን ፖሊሶች ጭምር ወደ ኮሌጁ ሲመጡ ከካፍቴሪያው የመስተንግዶ አገልግሎት ሲያገኙ የቆዩ መሆኑን ጠቅሶ በወቅቱ ከፍተኛ የዋጋ ውጣ ውረድ የነበረ በመሆኑና አንዳንድ ጊዜ ሰራዊቱ ከግዳጅ መልስ በእኩለ ለሊት ጭምር የምግብና የትኩስ መጠጥ መስተንግዶ ይሰጥ ስለነበረ ካፍቴሪያው ሳይመዘግባቸው የቀሩ አገልግሎቶች ስላሉ ኮሌጁ ካፍቴሪያውን እንዲደጎም በጠየቀው መሰረት ኮሌጁ ከውስጥ ገቢ ብር 15,000.00 ለካፍቴሪያው የድጎማ ክፍያ ፈጽሞ ተገኝቷል።

4.5.2. <u>ሥጋት</u>

ለካፍቴሪያ ድጎማ ተብሎ የተያዘ በጀት ሳይኖር እና በሚመለከተው አካል ሳይፈቀድ የድጎማ ክፍያ መፈጸም ለመንግሥት ገንዘብ አለአግባብ መውጣት ምክንያት ሊሆን ይችላል።

4.5.3. <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

በመንግሥት ላልተፈቀደና በጀት ላልተያዘለት ወጪ ክፍያ መፈጸም አግባብ ባለመሆኑ ክፍያው ተመላሽ ተደርጎ ፈሰስ መደረግ ይኖርበታል። ለወደፊቱም በክፍያ አፈጻጸም ላይ ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ ይኖርበታል።

4.5.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ

የድጐማ የተከፈለው ብር 15,000.00 በሥራ አመራሩ በቃለ-ጉባኤ ተወስኖ ሊከፈል ችሏል። ለወደፊቱ እርምት ወስደን የምናስተካክል መሆኑን እንገልጻለን።

4.5.5. የኦዲተሩ አስተያየት

ያለአግባብ ካፍቴሪያ ድጎማ ተብሎ ከውስጥ ገቢ በጀት የተከፈለው ገንዘብ ለመንግስት ተመላሽ መደረግ ይኖርበታል። ለወደፊቱም በጀት ላልተያዘላቸው ወጪዎች ክፍያ እንዳይፈጸም ከፍተኛ ጥንቃቄ መደረግ ይኖርበታል።

4.6. የግንባታ ሥራው በተቋረጠበት ጊዜ የተከፈለ የማማከር ክፍያ፤

4.6.1. ግኝት

ኮሌጁ የፈጸማቸው ማማከር ሥራ ክፍያዎች በውሉ መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ኮሌጁ ከሳምሶን ገ/ዮሀንስ ጋር ተዋዉሎ የሚያሰራውን የሰራተኞች መኖሪያ ቤት የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ዲዛይን አክስዮን ድርጅት የማማከሩን ስራ እንደሚሰራ የሚታወቅ ቢሆንም ኮንትራክተሩ የኮንስትራክሽን ስራዉን ሳይጨርስ አቋርጦ ከወጣ ከአመት ከስድስት ወር በላይ ሆኖት እያለ ድርጅቱ አገልግሎቱን ላልሰጠበት የማማከር ክፍያ በሚል ብር **115,469.70** ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ ታውቋል። (ለዝርዝሩ አባሪ 8 ተያይዟል)

4.6.2. ሥጋት

- ☞ የመንግሥት ገንዘብ ያለአግባብ ወጪ ሊሆን ይችላል።
- ☞ ያለአግባብ ክፍያ መፈጸም ተጠያቂነትን ሊያመጣ ይችላል።

4.6.3. <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

ኮንትራክተሩ ግንባታውን አቋርጦ የወጣ በመሆኑ ኮሌጁ ለማማከር ስራ ከኢትዮጵያ የኮንስትራክሽን ዲዛይን አክስዮን ድርጅት ጋር የገባውን ዉል ማቋረጥ ይኖርበታል።

4.6.4. <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

የህንጻ ተቋራጩ ሥራውን ያቋርጥ እንጂ ህንጻ ዲዛይን የማማከር ስራውን አላቋረጠም። በዚህም ምክንያቱም የአድሚንስትሬሽን ክፍያ ቀርቶ የማማከር ክፍያውን ብቻ የከፈልን መሆኑን እንገልፃለን።

4.6.5. <u>የኦዲተሩ አስተያየት</u>

ሳምሶን ህንጻ ተቋራጭ ድርጅት የግንባታ ስራውን ሳይጨርስ አቋርጦ ከወጣ ከዓመት ከስድስት ወራት በላይ ሆኖት እያለ ህንጻ ተቋራጩ ስራውን ቢያቋርጥም የማማከር ስራውን አላቋረጠም ተብሎ የተሰጠው ምክንያት ተቀባይነት የሌለው መሆኑ ሊታወቅ ይገባል። ከአማካሪው ድርጅት ጋር ውል የተገባው ህንጻ ተቋራጩ እንዲያማክርና ሥራውን እንዲቆጣጠር መሆኑ ይታወቃል። ስለዚህ ህንጻ ስራ ተቋራጩ ስራውን ካቆመ በኋላ አማካሪው ማንን እንደሚያማክር ግልጽ አይደለም። ኮሌጁም ቢሆን በምን አግባብ ለማማከር አገልግሎት ክፍያ እንደፈጸመ ግልጽ አይደለም። በመሆኑም ከላይ በማሻሻያ ሀሳቡ ላይ በተመለከተው መሰረት አለአግባብ እየተፈጸመ የሚገኘው ክፍያ በአስቸኳይ እንዲቆም መደረግ ይኖርበታል።

5. <u>ንብረት</u>

5.1. <u>በንብረት አያያዝ ላይ የታዩ ክፍተቶች</u>፤

5.1.1. <u>ግኝት</u>

የኮሌጁ የንብረት አስተዳደር በመንግሥት የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 እና በተጨማሪም ይህንኑ ለማስፈፀም በወጣው የመንግሥት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 መሰረት የሚፈጸም መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

1. <u>**በቋሚና አላቂ ዕቃ ግምጃ ቤት**</u>

   ጊዜ ያለፈባቸውና አገልግሎት የማይሰጡ 12 ኦቨርሄድ ፕሮጀክተሮች፣ 12 ፕሪንተሮች፣ አንድ የቡና ማሽን እና በርካታ ጄነራል ጆርናል ፓዶች ያለአገልግሎት ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፤

2. <u>**በኮሌጁ ክሊኒክ**</u>

   በርካታ የህክምና ዕቃዎች ቢኖሩም በሰለጠነ የሰው ኃይል ምክንያት ያለአገልግሎት ታሽጎባቸው የሚገኙ መሆኑ፤ (በ2006 እና በ2008 በጀት ዓመት ኦዲት ወቅትም አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም በድጋሚ ተገኝቷል)

3. ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ የተደረገ ቢሆንም ቆጠራው በመዝገብ ላይ (በእስቶክ ካርድ) ላይ ከተመለከተው ከወጪ ቀሪ ጋር እንዲመዛዘን ያልተደረገ መሆኑ፤

4. በኮሌጁ የምርት ግምጃ ቤት የእህል ማድረቂያ ማሽን ለረጅም አመታት ያለ አገልግሎት በግምጃ ቤት ውስጥ የሚገኝ መሆኑ፤

5. በእርዳታ እና በስጦታ የገቡ እቃዎች ዋጋ ያልተተመነላቸው መሆኑ፤

6. በኮሌጁ ያሉት ከብቶች ከኮሌጁ ውጪ ካሉት ከብቶች ጋር የሚገናኙ መሆኑ፣

ታውቋል። በአብዛኛዎቹ ላይ ባለፉት በጀት ዓመታት ኦዲት ወቅትም እርምጃ እንዲወሰድባቸው አስተያየት የተሰጠባቸው ቢሆንም እርምጃ ሳይወሰድባቸው ይገኛሉ።

5.1.2. <u>*ሥጋት*</u>

ኮሌጁ መንግሥት ባወጣዉ የንብረት አስተዳደር አዋጅና መመሪያ መሰረት የማይፈጸም ከሆነ፡-

- ለንብረት ቁጥጥር ሥርዓት መዳከም ምክንያት ሊሆን ይችላል።
- የመንግሥት ንብረት ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል።

☞ የኮሌጁ ከብቶቹ ከኮሌጁ ዉጪ ከሚገኙ ከብቶች ጋር የሚገናኙ ከሆነ ለበሽታ ሊጋለጡ ይችላሉ።

5.1.3. <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

የንብረት አስተዳደሩ መንግሥት ባወጣው የንብረት አያያዝና አጠቃቀም መመሪያ መሠረት እንዲስተካከልና እንዲፈጸም ትኩረት ተሰጥቶት ተገቢው ሥራ መሰራት ይኖርበታል።

5.1.4. <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

1. የቋሚና አላቂ ዕቃ ግምጃ ቤት ይገኙ የነበሩት ፕሮጀክተሮች፣ ላፕቶፕ፣ ዲስክቶፕ የመሣሰሉትን ተጠግነው አገልግሎት እንዲሰጡ ተደርጓል።

2. በኮሌጁ ክሊኒክ የተቀመጡት የህክምና ዕቃዎች ለሥራ የሚፈለጉ ቢሆንም የላብራቶሪ ባለሙያ ቅጥር ወጥቶ ማግኘት አልተቻለም። አሁንም በድጋሚ በጋዜጣ ታህሳስ 19 ቀን 2010 ዓ.ም አየር ላይ ይገኛል።

3. በዋጋ ተማኝ ኮሚቴ በርካታ ንብረት ተተምኖ በእያንዳንዱ ስቶክ ካርድ ላይ ምዝገባዉን የመመዝገብ ሥራ በሂደት ላይ ይገኛል።

3. በተራ ቁጥር 3, 4 እና 6 ለተመለከቱት ምላሽ አልተሰጠባቸውም።

5.1.5. <u>የኦዲተሩ አስተያየት</u>

ተጠግነው አግልግሎት ላይ እንዲውሉ መደረጉ የሚበረታታ ሲሆን ተጠግነው አግልግሎት ላይ ለመዋላቸው ግን በቀጣይ ኦዲት ወቅት የሚረጋገጥ ይሆናል። ሆኖም ኮሌጁ የንብረት አስተዳደሩን መንግሥት ባወጣው የንብረት አያያዝና አጠቃቀም መመሪያ መሠረት እንዲፈጸም ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ይኖርበታል።

5.2. <u>የተሽከርካሪ ስምሪት፣ አያያዝና አጠቃቀም ላይ የታዩ ክፍተቶች</u> ፤

5.2.1. <u>ግኝት</u>

የኮሌጁ የተሽከርካሪ ሥምሪት፣ አያያዝና አጠቃቀም በፌዴራል መንግሥት የተሽከርካሪዎች ስምሪትና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 32/2004 መሰረት መፈጸሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፦

- መሥሪያ ቤቶች የተሽከርካሪዎችን የነዳጅ ፍጆታ ለመከታተልና መዝግቦ ለመያዝ እንደደረጃቸው የተሽከርካሪዎች የኪሎ ሜትር ቆጣሪ ጌጅ የተሟላና በትክክል የሚሰራ መሆኑን በየጊዜው በመከታተል ማረጋገጥ እንዳለባቸው የሚደነግግ ቢሆንም ሁለት መኪናዎች ታርጋ ቁጥራቸው ኢ.ት. 00703፣ እና ኢ.ት 4-01127፣ የኪሎ ሜትር ቆጣሪ ጌጃቸው የማይሰራ መሆኑ፤
- የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር ወይም ሊብሬ ያልቀረበላቸው አምስት ተሽከርካሪዎች የሚገኙ መሆኑ፤ (የሰሌዳ ቁጥር ኢ.ት 4-02480፣ ኢ.ት 4-4376 እና ኢ.ት 4-4377 እንዲሁም አንድ ባጃጅ እና አንድ ትራክተር ሰሌዳ ቁጥር የሌላቸው መሆኑ)
- አገልግሎት የማይሰጡ 6 ተሽከርካሪዎች ተጠግነው አገልግሎት ላይ እንዲውሉ ወይም እንዲወገዱ ያልተደረጉ መሆኑ፤
  (የሰሌዳ ቁጥራቸውም፦ ኢ.ት 4-24817፣ ኢ.ት 4-24818፣ ኢ.ት 4-01452 ኢ.ት 4-13390፣ ኢ.ት 4-0788 እና ኢ.ት 4-0744)
- በኮሌጁ ስም የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር ያልተዘጋጀላቸው ሰባት ተሽከርካሪዎች የሚገኙ መሆኑ፤ (ለዝርዝሩ አባሪ 9 ተያይዟል)

ታውቋል። በአብዛኛዎቹ ግኝቶች ላይ በ2008 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ወቅትም አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም የማስተካከያ በተሟላ ሁኔታ እርምጃ አልተወሰደም።

5.2.2. ሥጋት

- ☞ በወጣው የተሽከርካሪዎች መመሪያ መሰረት ያለመፈጸም በውስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱ ላይ ክፍተት ሊፈጥር ይችላል።
- ☞ መወገድ ያለባቸው ንብረቶች በወቅቱ ካልተወገዱ ለከፋ ብልሽት ሊዳረጉና ዋጋቸው ሊቀንስ እንዲሁም በቀላሉ ለጥፋትና ለብክነት ሊዳረጉ ይችላሉ።
- ☞ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር የሌላቸው ንብረቶች እንዲሁም የባለቤትነት መታወቂያ ደብተራቸው በሌሎች መሥሪያ ቤቶች የሆኑ ተሽከርካሪዎች የኮሌጁ ንብረቶች ናቸው ብሎ ለመቀበል ሊያስቸግር ይችላል።

5.2.3. የማሻሻያ ሃሳብ

- ✓ በመመሪያው መሰረት እያንዳንዱ ተሽከርካሪ የኪሎ ሜትር ቆጣሪ ጌጅ የተሟላና በትክክል የሚሰራ መሆኑን በየጊዜው በመከታተል እንዲረጋገጥ፤
- ✓ መወገድ ያለባቸው ተሽከርካሪዎች በመመሪያው መሰረት እንዲወገዱ፣ ተጠግነው አገልግሎት መስጠት የሚችሉት ደግሞ እንዲጠገኑ፤
- ✓ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር የሌላቸው ንብረቶች እንዲሁም የባለቤትነት መታወቂያ ደብተራቸው በሌሎች መሥሪያ ቤቶች የሆኑ ተሽከርካሪዎች በኮሌጁ ሥም የባለቤትነት ደብተር እንዲሊወጣላቸው፤

መደረግ ይኖርበታል።

5.2.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ

- ♦ መጠገን የሚገባቸውን እናስጠግናለን። ሊብሬና ታርጋ የሌላቸውን በተደጋጋሚ ጥረት ቢደረግም ሊገኝላቸው አልተቻለም። የተቀሩትን ለማስጠት ጥረት እየተደረገ ይገኛል። ሌሎች የባለቤትነት ደብተር የሌላቸውንም ንብረትነታቸው ወደ ኮሌጁ እንዲዞር ጥረት እየተደረገ ይገኛል።

- ወደፊት የማስጠገን ስራውን የምንሰራ ይሆናል።

- የሠሌዳ ቁጥር ኢ.ት 4-4377 ሞተር ሳይክልና አንድ ሚስ ትራክተር በስጦታ ከዋናው መሥሪያ ቤት የተገኙ ሲሆኑ በወቅቱ ሊብሬና ታርጋቸው አብሮ ያልተሰጠን ቢሆንም በተደጋጋሚ እንዲሰጠን በደብዳቤም ሆነ በአካል በመገኘት ብንጠይቅም እስከ አሁን ድረስ ለማግኘት አልቻልንም።

- የሠሌዳ ቁጥር 4-02480 ዲፌንደር መኪናም ከዋናው መሥሪያ ቤት ሊብሬውን ፈልገን እንሰጣችኋለን በሚል ምላሽ የተሰጠን ሲሆን እስከ አሁን ድረስ ሊልኩልን አልቻሉም። መረጃዎቹን ለማግኘት አዲስ አበባ አስሩም ክፍለ ከተማ ማስረጃ እንዲሰጡን ጥያቄ አቅርበን ማግኘት አለመቻላቸውን አረጋግጠውልናል። (ተሽከርካሪዎቹ ከሰላሳ አመት በላይ ያገለገሉ በመሆኑ መረጃውን ማግኘት አልተቻለም) ካልሆነ ግን ኮሌጁ በራሱ አካሄድ ሊብሬ ያወጣለታል።

- ባጃጁን ወደ አዋሳ መንገድ ትራንስፖርት ጽህፈት ቤት ወስዶ ሊብሬና ታርጋ ለማውጣት ከአንዴም ሁለቴ ጥረት ተደርጎ ባጃጁ ተጭኖ መሄድ ስላለበት በኮሌጁ መለስተኛ የጭነት መኪና ተጭኖ መንገድ ላይ የመኪናው ካሶኒ ባጃጁን መሽከም አቅቶት በመቦደሱ ወደ ግቢ የተመለሰ ሲሆን አስተያየቱ (ጥያቄው) ተገቢነት ያለው ስለሆነ አሁንም በአፋጣኝ ሊብሬና ታርጋ እንዲወጣለት እናደርጋለን።

- የሠሌዳ ቁጥር ኢ.ት 4-24817፣ ኢ.ት 4-24818 ፊያት መኪኖች፣ መረጃዎቹ ተጠናክረው ለመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ተልኳል።

- ኢ.ት 4-01452፣ ኢ.ት 4-13390 ዳዎ ገልባጭ መኪና ፣ ኢ.ት 4-0788 ሞተር ሳይክልና ኢ.ት 4-0744 ሞተር ብስክሌቶች ሳይወገዱ የቆዩት ተሽከርካሪዎችን ለማስወገድ ከ4 ዓመት በፊት ጥረት የተጀመረ ቢሆንም መኪኖቹ ከዋናው መስሪያ ቤት በስጦታ የተሰጡ ስለነበርና

የመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎትም የተሟላ መረጃ ካላመጣችሁ ለማስወገድ እንቸገራለን በማለቱ ይህን ጠቅሰን ለዋናው መስሪያ ቤት በተደጋጋሚ የፃፍናቸው ደብዳቤዎች ምላሽ በማጣታቸው እስከአሁን ሳይወገዱ ቀይተዋል። በተጨማሪም ለግዥ ንብረት ማስወገድ አገልግሎት በሰነድ አልባነት እንዲወገዱልን በደብዳቤ ጥያቄ ያቀረብን ሲሆን፣ ለዚህም በአዲስ አበባ ትራንስፖርት ቅ/ጽ/ቤት በሁሉም ክፍለ ከተማ ማስረጃ እያሰባሰብን እንገኛለን። በዚህም ከሰሌዳ ቁጥር 4-24817 እና 4-24818 ዉጪ የሌሎቹን መረጃዎች ማግኘት አልተቻለም። የሰሌዳ ቁጥር 4-13390 ኢት ዳዋ ገልባጭ መኪና በደረሰበት የግጭት አደጋ በኢትዮጵያ መድን ድርጅት እንዲጠገን የገባ ሲሆን ከደረሰበት ከፍተኛ ጉዳት አንጻር በሙሉ ውድመት ክፍያውን ለመፈጸም ተሽከርካሪው ከዕዳና እገዳ ነጻ ስለመሆኑና ቀረጥ የተከፈለበት ስለመሆኑ በተጠየቅነው መሰረት መረጃውን አሟልተን ያቀረብን ሲሆን አፈጻጸሙ በሂደት ላይ ይገኛል።

- በመጨረሻ ዝርዝራቸው የተጠቀሱት ተሽከርካሪዎች በኮሌጁ ስም የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር የላቸውም የተባለው ትክክል ስለሆነና ወደ ኮሌጁ ስም መዞር እንደሚገባቸው የተረዳነው በቅርቡ ስለሆነ አስተያየቱን በገንቢነቱ ተቀብለን የማስተካከያ እርምጃ የምንወስድ መሆኑን እንገልጻለን።

5.2.5. <u>የኦዲተሩ አስተያየት</u>

የተሽከርካሪዎቹ የኪሎ ሜትር ቆጣሪ ጌጅ እንዲሰራ፤ ሊብሬ የሌላቸው ተሽከርካሪዎች ሊብሬ እንዲወጣላቸው፤ መወገድ ያለባቸው ተሽከርካሪዎችን መረጃዎች ለማሰባሰብ እና እንዲወገዱ ለማድረግ እየተደረገ ያለው ጥረት ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል። የተወሰዱት እርምጃዎችም በቀጣይ ኦዲት ወቅት የሚረጋገጡ ይሆናል።

6. <u>በጀት</u>

6.1. <u>ለየሂሳብ ኮዶቹ ከተደለደለ በጀት ከ10% በላይ ያልተሰራበትና ከበጀት በላይ የወጣ ሂሳብ</u>፤

6.1.1. <u>ግኝት</u>

ለኮሌጁ ለ2009 በጀት ዓመት ለየፕሮግራሞቹ የተፈቀደው የውስጥ ገቢና የካፒታል የወጪ በጀት በሥራ ላይ ከዋለው ጋር ሲነጻጸር ከ10% በላይ፡-

- ከካፒታል በጀት ብር **675,639.17**፣
- ከውስጥ ገቢ በጀት ብር **874,173.56**፣

በድምሩ ብር **1,549,812.73** ሥራ ላይ ያልዋለ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ከካፒታል በጀት ብር **11,997.65** ለየሂሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀት በላይ ወጪ መደረጉ ታውቋል። (ለዝርዝሩ አባሪ 10 ተያይዟል)

6.1.2. <u>ሥጋት</u>

- ☞ የወጪ ሂሣብ በጀቱ በእቅዱ መሠረት አለመፈፀሙ የኮሌጁን ዓመታዊ የሥራ ውጤት ዝቅ የሚያደርግ ከመሆኑም በተጨማሪ የበጀት ዕቅዱን ትክክለኛነት ላያመለክት ይችላል።
- ☞ በበጀት ሕጉ መሰረት የበጀት ዝውውር ሳይጠየቅ ለየሂሳብ ኮዶቹ ከተፈቀደው በጀት በላይ መጠቀም ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል።

6.1.3. <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

ኮሌጁ የበጀት ዕጥረት ካጋጠመው በቅድሚያ የበጀት ሕጉን ተከትሎ የበጀት ዝውውር መጠየቅ ይኖርበታል። ከዚህም በተጨማሪ ሐገሪቷ ያላትን ውስን በጀት በማብቃቃት በተገቢው ሥራ ላይ ማዋል ይቻል ዘንድ በተለይም በኀላ ሁኔታ ጥቅም ላይ ሳይውሉ በቀሩት የሂሳብ ኮዶች ላይ በበጀት እቅድ ዝግጅትና አጠቃቀም ወቅት ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል።

6.1.4. <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

- በካፒታል በጀት ላይ በተዘረዘሩት የበጀት ኮዶች ላይ የታየው ከታቀደው ከበጀት በታች የሆነው ወይም ያልተጠቀምንበት ምክንያት በገ/ኢ/ት/ሚኒስቴር በወቅቱ በጀት ባለመለቀቁ፤ በየበጀት ኮዱ ሰነድ ሳያስፈልግ በየወሩ 1/12 አለመላኩ አንዳንድ የአገልግሎት ክፍያዎች ከተያዘው (ከቀረው) በጀት በላይ የአገልግሎት ክፍያ በመጠየቃቸው ምክንያት ሲሆን፣ በተጨማሪም በችሮታ ጊዜ ክፍያ ተጠይቆባቸው በገ/ኢ/ት/ሚኒስቴር ተቀባይነት ባለማግኘቱ ገንዘቡ ሳይፈቀድና ሳይላክ የቀረና ያልተጠቀምንበት መሆኑን እንገልፃለን።

- በበጀት ኮድ 6271 ላይ ብር 11,997.65 ከበጀት በላይ የሚታየው ሂሳብ ከበጀት በላይ ተጠቅመን ሳይሆን በአመቱ በበጀት ኮድ ከተያዘው በጀት ውጪ በማስተባበሪያ ጽህፈት ቤቱ በኩል በጀት ተፈቅዶላቸው ሁለተኛ በዲግሪያቸውን ለሚማሩ መምህራን (ለምርምር) የተከፈለ በመሆኑ በ6271 በጀት ኮድ ላይ የተመዘገበ ስለሆነ ከበጀት በላይ ያሳየ መሆኑን እንገልጻለን። ከማስተባበሪያ ጽህፈት ቤቱም ጋር ተነጋግረናል ወደፊት ማስተካከያ ይወሰድበታል።

- ከውስጥ ገቢ በጀት ላይ የታየው ተራፊ በጀት ትክክል ሆኖ በየበጀት ኮዱ ከተያዘው በጀት በታች ልንጠቀም የቻልንበት ምክንያት የእቃ አቅራቢዎችና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች እቃዎችንና አገልግሎቶችን በወቅቱ ባለማቅረባቸው፤ ተጨማሪ እቃዎችን እና አገልግሎቶችን ለማዘዝ ያለው ቀሪ በጀት ብቁ ባለመሆኑ ለገ/ኢ/ት/ሚኒስቴር ፈሰስ ለማድረግ የተገደድን መሆኑን እንገልጻለን።

  (በዝርዝር ለተሰጠው ምላሽ አባሪ 12 ተያይዟል)

6.1.5. <u>የኦዲተሩ አስተያየት</u>

ኮሌጁ የበጀት ዝውውር ሳያደርግ ለየሂሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀት በላይ መጠቀሙ አግባብነት የለውም። እንዲሁም ኮሌጁ በበጀት ዕቅድ ዝግጅትና አጠቃቀም ላይ ተገቢ የሆነ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርበታል። በተጨማሪም

መሥሪያ ቤቱ የበጀት አጠቃቀሙ ላይ ክትትል በማድረግ እና የማይጠቀምበትን በጀት ለይቶ በማውጣት የበጀት እጥረት ላለባቸው መሥሪያ ቤቶች የበጀት ዝውውር ተደርጎ ጥቅም ላይ እንዲውል በእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር በኩል የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር እንዲያውቀው መደረግ እንዳለበት ለማሳሰብ እንወዳለን፡፡

7. <u>ልዩ ልዩ</u>

7.1. <u>የሥጋት ተጋላጭነት ግምገማ ያልተደረገ ስለመሆኑ</u>፤

7.1.1. <u>ግኝት</u>

በፌዴራል መንግሥት የውስጥ ቁጥጥር ደረጃዎች መመሪያ ቁጥር 8/2003 መሰረት የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የተቋቋሙበትን ዓላማዎች ለማስፈጸም ዕቅዶችና ዝርዝር የዕለት ተዕለት ተግባራት በማከናወን ሂደት የሚከሰቱ ችግሮችንና የተጋላጭነት ደረጃ ለመለየት የውስጥና የውጪ ኦዲተሮችንና ሌሎች የሚመለከታቸውን ባለሙያዎች በመጠቀም የሥጋት ምንጮች ዳሰሳ ማካሄድ እንዳለባቸው ተመልክቷል፡፡ ሆኖም ኮሌጁ የሥጋት ምንጮች ዳሰሳ፣ የተጋላጭነት ደረጃ መለየት እና የሥጋት ተጋላጭነት ፍተሻ ያላደረገ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

7.1.2. <u>ሥጋት</u>

የሥጋት ተጋላጭነት ዳሰሳ ጥናት ተደርጎ የመፍትሄ አቅጣጫ ካልተቀመጠ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች ኮሌጁ ዓላማውን እንዳያሳካ እንቅፋት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

7.1.3. <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

ኮሌጁ የሥጋት ተጋላጭነት ዳሰሳ በየጊዜው ቢደርግ በውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ደካማነት የተነሳ ሊከሰቱ የሚችሉ ችግርችን ለይቶ ቅድመ ጥንቃቄ ለመውሰድ የሚኖረውን ጥቅም ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በመመሪያው መሰረት የሥጋት ተጋላጭነት ዳሰሳ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

ስለሆነም በመመሪያው መሰረት የስጋት ተጋላጭነት ዳሰሳ እንዲደረግ እናሳስባለን።

7.1.4. *የሥራ አመራሩ ምላሽ*

በኮሌጁ ተጨባጭ ሁኔታ ለሌብነት ለሙስናና ለብክነት እንደዚሁም ለመልካም አስተዳደር የቅሬታ መንስኤ ናቸው ተብለው የሚታወቁትን በመለየት ሁለት አይነት የማምከኛ ዕቅድ አውጥተን ለተግባራዊነቱ እንቅስቃሴ እየተደረገ ይገኛል ።

- ✓ የመልካም አስተዳደር ንቅናቄ ማጣጣያ ዕቅድ ትግበራ፣
- ✓ የአራት ዓመት (2009-2012) የሙስና መከላከል ስትራቴጂክ ዕቅድ የካቲት 3 ቀን 2009 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር 20/አር/ከ/7-37 እና ሰኔ 19 ቀን 2009 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር 192/አር/ከ/4-3 የተጻፈውን ማየት ይቻላል።

7.1.5. *የኦዲተሩ አስተያየት*

የሥጋት ተጋላጭነት ግምገማ የሚደረገው መሥሪያ ቤቱ የተቋቋመበትን ዓላማ ለማስፈፀም በሚያደርገው እንቅስቃሴ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ሥጋቶችን በመለየትና ምንጫቸውን በማወቅ፣ የሥጋት ደረጃና (Level of Risk) *የተጋላጭነት አቅም* (Probability of Occurrence) *ተገንዝቦ ይህንን ሥጋት ለመቀነስ ከተቻለም ለመከላከል የሚያስችል ሥርዓት ለመዘርጋት ነው። ሆኖም አሁን ኮሌጁ ያዘጋጀው የሙስና መከላከል ስትራቴጂክ ዕቅድ እንጂ የሥጋት ተጋላጭነት ግምገማ አይደለም። ስለሆነም መሥሪያ ቤቱ በመመሪያው መሠረት ተቋማዊ የሥጋት ተጋላጭነት ግምገማ ቢያደርግ ጠቃሚነቱ የጎላ መሆኑን ለመግለጽ እንወዳለን።*

7.2. በቅጥርና በዕድገት ያልተሞሉ ክፍት የሥራ መደቦችን በተመለከተ፤

7.2.1. ግኝት

ኮሌጁ በዕቅድ የያዛቸውን ተግባራት በአግባቡ ለመፈጸም ይችል ዘንድ ክፍት የሥራ መደቦችን በሰው ኃይል መሙላት እንዳለበት ይታመናል። ሆኖም መሥሪያ ቤቱ በመዋቅር ከተፈቀደለት 791 የስራ መደቦች ውስጥ

በሰው ኃይል የተሞላው 647 ሲሆን 144 (18%) የሥራ መደቦች ክፍት መሆናቸው ታውቋል።

7.2.2. ሥጋት

የተሟላ የሰው ኃይል ባለመኖሩ ምክንያት ኮሌጁ ዕቅዱን እንዳያሳካ ምክንያት ሊሆን እንዲሁም በአሰራር ላይ ክፍተት ሊፈጥር ይችላል።

7.2.3. የማሻሻያ ሃሳብ

ኮሌጁ የተሰጠውን ኃላፊነት በአግባቡ ለመወጣት ያስችለው ዘንድ ክፍት የስራ መደቦችን በቅጥርና በእድገት እንዲሞሉ ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ይኖርበታል።

7.2.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ

ከፍተኛ ክፍት የሥራ መደቦችን ቅጥር ለመፈጸም በጀት የተለቀቀልን ግንቦት መጨረሻ በመሆኑ የበጀት መዝጊያ የጊዜ ጥበት ስለገጠመን ቅጥሩን ማከናወን ያልቻልን ሲሆን በቀጣይ አስፈላጊውን ማስተካከያ ለማድረግ እየሰራን መሆኑን እየገለጽን፤ በዝቅተኛ የሥራ መደቦች ላይ በርካታ የሥራ መደቦችን በቅጥርና በደረጃ እድገት ለመሙላት በሂደት ላይ እንገኛለን።

በመጨረሻም በኦዲት ወቅት በኮሌጁ ኃላፊዎችና ሰራተኞች ስለተደረገልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን።

አባሪ. 1

የሂሳብ መደቡን ጠብቆ ያልተመዘገበ ከሲኦሲ (COC) ምዘና የተሰበሰበ የገቢ ሂሳብ፤

ቀን	የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ ቁጥር	ገቢው የተመዘገበበት የሂሳብ መደብ	ገቢው መመዝገብ የነበረበት	የገንዘቡ ልክ	
29/05/2009	**RV 700851**	**1489**	**1443**	**3,000**	**00**
29/05/2009	**RV 700852**	**1489**	**1443**	**3,000**	**00**
29/05/2009	**RV 700857**	**1489**	**1443**	**3,000**	**00**
29/05/2009	**RV 700858**	**1489**	**1443**	**3,000**	**00**
30/05/2009	**RV 700882**	**1489**	**1443**	**3,000**	**00**
30/05/2009	**RV 700861**	**1489**	**1443**	**3,000**	**00**
30/05/2009	**RV 700868**	**1489**	**1443**	**3,000**	**00**
ድምር				**21,000**	**00**

አባሪ. 2

የተሰብሳቢ ሒሳብን የቆይታ ጊዜ የሚያሳይ ዝርዝር፤

ተራ ቁጥር	የሂሳብ መደብ ቁጥር	የተሰብሳቢ ሂሳቡ ክፍያ የቆይታ ጊዜ	የቆይታው ጊዜ		ድምር
			ከአንድ ወር አስከ አንድ ዓመት ድረስ የቆየ	ከአንድ ዓመት በላይ አስከ አምስት ዓመት ድረስ የቆየ	
I.	ከካፒታል በጀት				
1	4203	ከ2007 እስከ 2009 በጀት ድረስ		8,000.00	8,000.00
II.	ከውስጥ ገቢ				
2	4274	ከ2007 እስከ 2009 በጀት ድረስ	62,582.88	73,428.77	136,011.65
		ድምር	62,582.88	81,428.77	144,011.65

አባሪ. 3

<u>የተከፋይ ሒሳብን የቆይታ ጊዜ የሚያሳይ ዝርዝር፤</u>

ተራ ቁጥር	የሂሳብ መደብ ቁጥር	የተከፋይ ሂሳቡ የቆይታ ጊዜ	የቆይታው ጊዜ			ድምር
			ከአንድ ወር አስከ አንድ ዓመት ድረስ የቆየ	ከአንድ ዓመት በላይ አስከ አምስት ዓመት ድረስ የቆየ	ከአምስት ዓመት በላይ አስከ አስር ዓመት ድረስ የቆየ	
I.	**የካፒታል ሂሳብ**					
1.	**5002**	ከ2007 እስከ 2009 በጀት ድረስ		8,000.00		8,000.00
II.	**የውስጥ ገቢ ሂሳብ**					
2.	**5002**	ከ2008 እስከ 2009 በጀት ድረስ	34,643.49			34,643.49
		ጠቅላላ ድምር	34,643.49	8,000.00		42,643.49

አባሪ. 4

በተገቢው የሂሳብ መደብ ያልተመዘገቡ የወጪ ሂሳቦችን በተመለከተ፤

ቀን	የገቢው ምክንያት	የባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር	የወጪ ሂሳቡ የሂሳብ ኮድ		የገንዘቡ ልክ	
			የተመዘገበበት	መመዝገብ የነበረበት	ብር	ሳ
05/03/09	ለማስጫኛና ማውረጃ	BPV075512	6114	6255	23,760	00
07/04/09	ለማስጫኛና ማውረጃ	BPV075660	6114	6255	118,615	42
07/04/09	ለማስጫኛና ማውረጃ	BPV075660	6114	6255	23,760	00
26/05/09	ለማስጫኛና ማውረጃ	BPV075760	6114	6255	92,253	70
16/08/09	ለማስጫኛና ማውረጃ	BPV0744188	6114	6255	8,888	00
30/08/09	ለቋሚ ሰራተኛ የጡረታ መዋጮ	JV 71903	6231	6131	195,953	35
ድምር					463,230	47

አባሪ 5

በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ላይ ተመዝግበው የተገኙ የጥሬ ገንዘብ ክፍያዎች ዝርዝር፤

ተራ ቁጥር	ቀን	የሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር	የወጪዉ ምክንያት	ሂሳብ መደብ	የገንዘብ መጠን በዴቢት		የገንዘብ መጠን በክሬዲት	
					ብር	ሳ	ብር	ሳ
1	19/01/2009	71658	የስልክ ክፍያ	6258 4101	20,583	92	20,583	92
2	23/01/2009	71659	የመብራት ክፍያ	6257 4101	31,938	91	31,938	91
3	18/04/2009	71730	የመብራት ክፍያ	6257 4101	30,694	57	30,694	57
4	22/05/2009	71741	የቀን ሰራተኛ ሚንዳ	6114 4101	14,910	00	14,910	00
5	10/06/2009	71746	የኢንተርኔት ክፍያ	6258 4101	14,717	70	14,717	70
6	13/06/2009	71747	የቀን ሰራተኛ ሚንዳ	6114 4101	21,435	00	21,435	00
7	15/06/2009	71748	የውሃ ክፍያ	6259 4101	5,089	88	5,089	88
8	20/06/2009	71749	የስልክ ክፍያ	6258 4101	5,438	17	5,438	17
9	20/06/2009	71750	የመብራት ክፍያ	6257 4101	30,332	63	30,332	63
10	30/06/2009	71853	የስልክ ክፍያ	6258 4101	9,451	89	9,451	89
11	16/08/2009	71875	የስልክ ክፍያ	6258 4101	14,717	70	14,717	70
12	24/08/2009	71876	የመብራት ክፍያ	6257 4101	43,550	40	43,550	40
13	30/08/2009	71879	የኢንተርኔት ክፍያ	6258 4101	14,717	70	14,717	70
ድምር					**257,578**	**47**	**257,578**	**47**

<u>በፋይናንስ መመሪያው መሰረት ያልተመዘገበና ያልተፈጸመ የኮንትራክተር ክፍያ ዝርዝር፤</u>

I. ክፍያው የተፈጸመው፡ ሣይለም ኮንስትራክሽን ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር									
ቀን	**የባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ደረሰኝ ቁጥር**	**በመሥሪያ ቤቱ ሂሳብ ክፍል በየደረጃው ክፍያ ሲፈጸም የተመዘገበ**							
		በዴቢት			**በክሬዲት**				
		1	**2**	**3**	**4**	**5**	**6**	**7**	**8**
		6322	**4251**	**5061**	**5059**	**5006**	**4251**	**5061**	**4103**
26/10/07	**BPV 074520**		**2,049,790.00**						**2,049,790.00**
26/01/08	**BPV 074610**		**510,187.00**						**510,187.00**
04/05/08	**BPV 074852**	**1,340,290.87**	**1st payment**		**174,820.55**	**10,489.23**	**268,058.17**	**58,273.52**	**828,649.40**
05/08/08	**BPV 074996**	**1,062,044.39**	**2nd payment**		**138,527.53**	**8,311.65**	**632,817.55**	**46,175.84**	**236,211.82**
17/10/08	**BPV 075168**	**823,960.64**	**3rd payment**		**107,473.13**	**6,448.39**	**308,985.24**	**35,824.38**	**365,229.50**
30/12/08	**BPV 075311**	**692,573.37**	**4th payment**		**90,335.66**	**5,420.14**	**259,715.02**	**30,111.88**	**306,990.67**
21/04/09	**BPV 075704**	**736,845.94**	**5th payment**		**96,110.34**	**5,766.62**	**276,317.22**	**32,036.78**	**326,614.98**
02/09/09	**BPV 0744218**	**1,475,978.19**	**6th payment**		**192,518.90**	**11,551.13**	**414,741.49**	**32,992.66**	**824,174.01**
ድምር		**6,131,693.40**	**2,559,977.00**		**799,786.11**	**47,987.16**	**2,160,634.69**	**235,415.06**	**5,447,847.38**

II. ክፍያው የተፈጸመው፡ ሣይለም ኮንስትራክሽን ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር				
የውል ዋጋ የተጨማሪ ዕሴት ታክስን ጨምሮ ↔	**8,533,254.15**	**የውል ዋጋ ቫትን ሳይጨምር ↔**	**7,420,221.00**	
ቅድሚያ ክፍያ የተሰጠው ፐርሰንት ፡ 30 %				
የቅድሚያ ክፍያ ተመላሹ ፐርሰንት፡ 37.50 %				

ቀን	**የባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ደረሰኝ ቁጥር**	**ሊከናወን የሚገባው ምዝገባ**						
		በዴቢት		**በክሬዲት**				
		1	**2**	**3**	**4**	**5**	**6**	**7**
		6322	**4251**	**5059**	**5006**	**4251**	**5061**	**4103**
26/01/08	**BPV 074610 Advance**		**2,559,976.24**	**333,909.94**	**0.00**	**0.00**	**0.00**	**2,226,066.30**
21/04/09	**Payment Certificate No 5** **Work executed to date (BPV 0744218)**	**6,131,693.40**		**499,866.31**	**47,987.16**	**2,299,385.03**	**266,595.37**	**3,017,859.53**
ድምር		**6,131,693.40**	**2,559,976.24**	**833,776.25**	**47,987.16**	**2,299,385.03**	**266,595.37**	**5,243,925.83**

ማጠቃለያ															
III. **ክፍያው የተፈጸመው ድርጅት ሥም ፡ ሣይለም ኮንስትራክሽን ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኀበር**															
በመስሪያ ቤቱ ሂሳብ ክፍል በየደረጃው ክፍያ ሲፈጸም የተደረገ አጠቃላይ ምዝገባ					ሊከናወን የሚገባው ምዝገባ				ማስተካከያ ሊዘጋጅላቸው የሚገቡ ልዩነቶች						ምርመራ
የሒሳቡ መደብ	**ዴቢት**		**ክሬዲት**		**ዴቢት**		**ክሬዲት**		**የሒሳቡ መደብ**	**ዴቢት**		**ክሬዲት**			
6322	**6,131,693**	**40**			**6,131,693**	**40**			**6322**						
4251	**2,559,977**	**00**	**2,160,634**	**69**	**2,559,976**	**24**	**2,299,385**	**03**	**4251**			**138,751**	**10**		ያልተመለሰ የቅድሚያ ክፍያ ተመላሽ በመሆኑ ነው፡ ፡
5059			**799,786**	**11**			**833,776**	**25**	**5059**			**33,990**	**14**		ያልተቀነሰ የተጨማሪ ዕሴት ታክስ በመሆኑ ነው፡ ፡
5006			**47,987**	**16**			**47,987**	**16**	**5006**						
5061			**235,415**	**06**			**266,595**	**37**	**5061**			**31,180**	**31**		ያልተቀነሰ የመያዣ ሂሳብ በመሆኑ ነው፡ ፡
4103			**5,447,847**	**38**			**5,243,925**	**83**	**4103**	**203,921**	**55**				በብልጫ የተከፈለ የጥሬ ገንዘብ ሒሳብ በመሆኑ ነው፡፡
ድምር	**8,691,670**	**40**	**8,691,670**	**40**	**8,691,669**	**64**	**8,691,669**	**64**		**203,921**	**55**	**203,921**	**55**		

አባሪ. 7

በምርታማነት ማሻሻያ ማዕከል ለሾፌር መካኒክነት ለሰለጠኑ በብልጫ የተከፈለ የውሎ አበል ዝርዝር፤

ተራ ቁጥር	ስም	የወር ደመወዝ	የቀን ዉሎ አበል መጠን	አበል የተከፈለ የቀን ብዛት	በጠቅላላ የተከፈለው	የአስራ ስድስት ቀን መከፈል የነበረበት	በብልጫ የተከፈለ የአስራ ሁለት ቀን አበል
1	አቶ ጌትነት መንክር	2,872.00	165	28	4,685.25	2,640.00	2,045.25
2	አቶ ኤደቻ ጅማ	2,748.00	165	28	4,677.75	2,640.00	2,037.75
3	አቶ ገለቶ አያቶ	2,008.00	124	28	3,515.40	1,984.00	1,531.40
4	አቶ ሽፈራው አሰፋ	2,008.00	124	28	3,515.40	1,984.00	1,531.40
5	አቶ ጀማል ከዲር ኒኒ	1,511.00	124	28	3,503.00	1,984.00	1,519.00
6	አቶ ብርሃኑ ሁሪሳ	1,743.00	124	28	3,515.40	1,984.00	1,531.40
7	አቶ ባሳዝን ኤደኦ	2,197.00	124	28	3,503.00	1,984.00	1,519.00
8	አቶ ናፍያዲ ዑስማን	2,008.00	124	28	3,503.00	1,984.00	1,519.00
9	አቶ ጥላሁን ደሳለኝ	2,100.00	124	28	3,490.60	1,984.00	1,506.60
10	አቶ መኮንን ብርሃኔ	1,370.00	124	28	3,490.60	1,984.00	1,506.60
11	አቶ ታደሰ ኃ/ወልድ	1,370.00	124	28	3,490.60	1,984.00	1,506.60
	ድምር				40,890.00	23,136.00	17,754.00

አባሪ. 8

<u>የግንባታው ሥራው በተቋረጠበት ጊዜ የተከፈለ የማማከር ክፍያ</u>፤

የባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር	ቀን	የወጪው ምክንያት	በወጪ የተያዘበት ሂሳብ መደብ	
			ሂሳብ መደብ	የገንዘብ መጠን
075663	**06/04/2009**	የኮንትራት አስተዳደር አገልግሎት ክፍያ ከሀምሌ 2008 እስከ ጥቅምት 2009 እና የሚያዝያ 2008	**6251**	**57,734.85**
0744187	**13/08/2009**	የኮንትራት አስተዳደር አገልግሎት ክፍያ ከህዳር እስከ ጥር 2009 ዓ.ም ድረስ	**6251**	**34,640.91**
0744451	**26/10/2009**	የኮንትራት አስተዳደር አገልግሎት ክፍያ ከመጋቢት እስከ ሚያዝያ 2009 ዓ.ም ድረስ	**6251**	**23,093.94**
ድምር				**115,469.70**

አባሪ. 9

<u>በኮሌጁ ሥም የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር ያልተዘጋጀላቸው ተሽከርካሪዎች ዝርዝር</u>፤

ተራ ቁጥር	የሰሌዳ ቁጥር	የመኪናው ዓይነት	የተሽከርካሪዎቹ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር በስማቸው የሚገኝ መሥሪያ ቤቶች ሥም
1.	ኮድ 4-00703 ኢ.ት	ኒሳን ጀርመን	የደን ክለላ ምዝገባና ቅየሳ ማኔጅመንት፣
2.	ኮድ 4-00218 ኢ.ት	ድርብ ተግባር ጃፓን	በግብርና ሚኒስቴር የካቲት 25 ህብረት ስራ ኢንስቲትዩት
3.	ኮድ 4-00576 ኢ.ት	ላንድሮቤር እንገሊዝ	ቡናና ሻይ ባለስልጣን የቡና ማሻሻያ ፕሮጀክት
4.	ኮድ 4-01451 ኢ.ት	ቶዮታ ጃፓን	የካቲት 25 ህብረት ስራ ኢንስቲትዩት
5.	ኮድ 4-01127 ኢ.ት	ላንድሮቨር እንግሊዝ	የቡና ተክል ማሻሻያ
6.	ኮድ 4-08108 ኢ.ት	ላንድሮቨር እንግሊዝ	አውሮፓ ዩኒየን
7.	ኮድ 4-1452 ኢ.ት	ድርብ ተግባር ጃፓን	የካቲት 25 ህብረት ስራ ኢንስቲትዩት

ከ10% በላይ ያልተሰራበት በጀትና ለየሂሳብ ኮዶቹ

ከተደለደለው በጀት በላይ የወጣ ሂሳብ ዝርዝር፤

የወጪ ሒሳብ መደብ	የተስተካከለ በጀት	በሥራ ላይ የዋለ በጀት	ለየሒሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው የወጪ ሂሳብ በጀት			
			ሥራ ላይ ያልዋለ	በላይ የወጣ	ሥራ ላይ ያልዋለ እና ከተደለደለው በጀት በላይ የወጣው በፐርሰንት (%)	ለልዩነቱ የተሰጠ ዝርዝር ምላሽ
I. የካፒታል በጀት						
የበጀት ኮድ 211-02-04-003 (1800)						
6218	**75,000.00**		**75,000.00**		**100**	ከ/ገ/ኢ/ት/ሚኒስቴር በወቅቱ በጀት ባለመለቀቁ ምክንያት የተረፈ ነው ፡፡
6232	**20,417.00**	**16,134.97**	**4,282.03**		**21**	በኮሌጁ የአገልግሎቱ ተጠቃሚ በመቀነሱ (በድርጅቱ ተሽከርካሪ በመጠቀም) ምክንያት የተረፈ ነው፡፡
6233	**155,000.00**	**104,503.02**	**50,496.98**		**33**	ከ/ገ/ኢ/ት/ሚኒስቴር በወቅቱ በጀት ባለመለቀቁ ምክንያት በችሮታ ጊዜም ተጠይቆ ያልተለቀቀ በመሆኑ ነው፡፡
6244	**141,500.00**		**141,500.00**		**100**	ከ/ገ/ኢ/ት/ሚኒስቴር በጀት ባለመለቀቁ ምክንያት በችሮታ ጊዜም ተጠይቆ ያልተለቀቀ በመሆኑ ነው፡፡
6251	**1,000,000.00**	**876,562.72**	**123,437.28**		**12**	ኮሌጁ ለሲኦሲ (COC) እና ለከተማ ልማትና ህንፃ ዲዛይን ተከፍሎ ቀጣይ የክፍያ ጥያቄ ባለመቅረቡ የተረፈ ነው ፡፡

የወጪ ሒሳብ መደብ	የተስተካከለ በጀት	በሥራ ላይ የዋለ በጀት	ለየሒሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው የወጪ ሂሳብ በጀት			
			ሥራ ላይ ያልዋለ	በላይ የወጣ	ሥራ ላይ ያልዋለ እና ከተደለደለው በጀት በላይ የወጣው በፐርሰንት (%)	ለልዩነቱ የተሰጠ ዝርዝር ምላሽ
6252	**350,000.00**	**183,720.00**	**166,280.00**		**48**	ኮሌጁ ለሚያሰለጥናቸው ተማሪዎች የተግባር ትምህርት ለትራንስፖርት ከተያዘው በጀት ለአሰሪው ድርጅት ተከፍሎ የቀረ በመሆኑ ነው፡፡
6253	**43,470.00**	**3,469.50**	**40,000.50**		**92**	ለአንድ ጊዜ የጨረታ ማስታወቂያ ክፍያ ከበጀት በታች በመሆኑ ነው፡፡
6255	**5,000.00**	**4,295.00**	**705.00**		**14**	የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ባለመኖሩ (ውስን) በመሆኑ ነው፡፡
6256	**145,000.00**	**78,901.42**	**66,098.58**		**46**	ለአገልግሎቱ ያለው በጀት ባለመብቃቱ ነው ፡፡
6259	**12,017.00**	**4,178.20**	**7,838.80**		**65**	የፖስታ የአገልግሎቱ ተጠቃሚነት ውስን በመሆኑ ነው፡፡
6271	**23,999.00**	**35,996.65**	**0.00**	**11,997.65**	**50**	
ድምር	**1,971,403.00**	**1,307,761.48**	**675,639.17**	**11,997.65**		
II. የውስጥ ገቢ በጀት						
የበጀት ኮድ 211-02-04-003 (1900)						
6241	**2,310,000.00**	**1,987,173.99**	**322,826.01**		**14**	ለጥገና ጋራዥ ለገቡ ተሽከርካሪዎችን ታሳቢ ተደርጎ የተያዘ ስሆን በጊዜ ከጋራዥ ባለመውጣታቸው ሳይከፈል የቀረ ነው፡፡

የወጪ ሒሳብ መደብ	የተስተካከለ በጀት	በሥራ ላይ የዋለ በጀት	ለየሒሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው የወጪ ሂሳብ በጀት			
			ሥራ ላይ ያልዋለ	በላይ የወጣ	ሥራ ላይ ያልዋለ እና ከተደለደለው በጀት በላይ የወጣው በፐርሰንት (%)	ለልዩነቱ የተሰጠ ዝርዝር ምላሽ
6311	**1,700,000.00**	**1,494,575.00**	**205,425.00**		**12**	ካሌብና ኤኤልቲ አቅራቢ ድርጅቶች ውል የገቡትን ዕቃ ባለማቅረባቸው ምክንያት ሌሎች ማሽነሪዎች ተገዝተው የተረፈ በመሆኑ ነው፡፡
6251	**147,785.00**	**115,469.70**	**32,315.30**		**22**	የከተማ ልማት ህንጻ ዲዛይን አክስዮን ማህበር ለአማካሪ ድርጅት (ለከተማ ልማት ህንጻ ዲዛይንና) ለሌሎች የማማከር አገልግሎት የተያዘ በጀት ሲሆን ከተከፈለው የተረፈ በመሆኑ ነው፡፡
6253	**135,000.00**	**99,652.56**	**35,347.44**		**26**	ለአንድ ጊዜ የማስታወቂያ ክፍያ ጥያቄ የቀረበው ከበጀት በታች በመሆነ ነው፡፡
6254	**85,000.00**	**73,041.59**	**11,958.41**		**14**	ለአንድ ጊዜ ክፍያ ጥያቄ የቀረበው ከበጀት በታች በመሆኑ ነው
6257	**504,000.00**	**240,795.27**	**263,204.73**		**52**	ለኢትዮጵያ መብራት ሀይል አገልግሎት ክፍያው የሚያስፈልገው ተከፍሎ የተረፈ በመሆኑ ነው፡፡
6259	**17,000.00**	**13,903.33**	**3,096.67**		**18**	ለአሳሳ ውሃ ልማት አገልግሎት ክፍያው የሚያስፈልገው ተከፍሎ የተረፈ በመሆኑ ነው፡፡
ድምር	**4,898,785.00**	**4,024,611.44**	**874,173.56**			
ጠቅላላ ድምር	**6,870,188.00**	**5,332,372.92**	**1,549,812.73**	**11,997.65**		

አባሪ. 11

<u>የተቋረጠውን ግንባታ የሚያሳይ ፎቶ</u>

በሥራ አመራር ሪፖርት በተጠቀሱት የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች አተገባበር መርዓ-ግብር

የኦዲት ተደራጊ መሥሪያ ቤት ስም:- ________________________

ኦዲት የተደረገው ሂሳብ በጀት ዓመት:- ________________________

የተዘጋጀበት ቀን:- _________________

ተራ ቁጥር	የኦዲት ግኝቶች	የተሰጡት የማሻሻያ ሃሳቦች	እስከአሁን የተወሰዱ ማስተካከያ እርምጃዎች	ቀሪ ማሻሻያ ሃሳቦች ተግባራዊ የሚደረጉበት ጊዜ	ኃላፊነት የተሰጠው የሥራ ክፍል	ምርመራ

ማሳሰቢያ:- ይህ መርዓ-ግብር እና የኦዲት ሪፖርቱ ለመ/ቤትዎ እንደደረሰ የተወሰዱ እርምጃዎች በአስቸኳይ ተሞልቶ በ15 ቀናት ውስጥ ለመ/ቤታችን ካልተመለሰ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በምናቀርበው ዓመታዊ ሪፖርት ውስጥ "ለኦዲት ሪፖርት ማሻሻያ ሃሳቦች አተገባበር መርዓ-ግብር መልስ ያልላኩ መሥሪያ ቤቶች" ዝርዝር ውስጥ እና እርምጃ አለመወሰዱ ተጠቅሶ ለምክር ቤቱ ሪፖርት የሚቀርብ መሆኑን እንገልፃለን።